## በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

(የትንሣኤ መልእክት)

*„ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን፤በዐቢይ ኃይል ወሥልጣን“*

*የተወደዳችሁ አባቶች መነኮሳትና ካህናት፤ ወንድሞች ዲያቆናት*
*ውድ መዘምራንና መዘምራት፤ የተወደዳችሁ ምእመናንና ምእመናት!*

ለሰው ልጆች ሁሉ ቤዛ ለመሆን በመስቀል ተሰቅሎ የሞተው፤ በማሕየዊ ሞቱ ሞትን የደመሰሰው፤ በቅድስት ትንሣኤው የመቃብርን አስፈሪ ግርማ ደምስሶ በድል አድራጊነት የተነሣው፤ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው የሁላችን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መዋዕለ ጾሙን በሰላም አስፈጽሞ፤ ጾመ ልጓሙን ፈቶ እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ፤ አደረሰን፤ በማለት በጀርመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በራሴም ስም ልባዊ ምኞቴን ልገልጽ እወዳለሁ።

ከጌታችን፤ ከአምላካችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በፊት የነበሩ ሕያዋንና ሙታን በድግዝግዝ ዓለም፤ በሞት ጥላና በጨለማ ውስጥ ይመላለሱ ነበር። በመሠረቱ የሰው ልጅ በአምላኩ አርያና አምሳል ሲፈጠር ለዘለዓለም በተድላ ገነት በፍስሐና በደስታ፤ በሰላምና በፍቅር እንዲኖር ነበር፤ ነገር ግን ጥንተ ጠላት ሰይጣን በአማጣበት ፈተና፤ ራሱም ወደ በሠራው ኃጢአት ከቀደመ ክብሩ ተዋረደ፤ ወደ ምድረ ፋይድ ወረደ። በእርሱ ምክንያት ምድር ተረገመች፤ እሾህና አሜከላ አበቀለች፤ በንፍር ውኃ ተዋጠች፤ በእሳተ ገሞራ ተቃጠለች፤ አባር ቸነፈር በዛባት። በዓለም ዙሪያ የተበተነው የሰው ልጅ በቋንቋ፤ በዝር፤ በጎሳና በነገድ እየተለያየ፤ አንዱ ሌላውን እያሰቃየ፤ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ ቀርቶ የዲያብሎስ ተገዥ ሆነ። በነፍሱና በሥጋው ሠራዊተ አጋንንት ሠለጠኑበት። በሕይወት ፈንታ ሞት፤ በክብር ፈንታ ውርደት፤ በበረከት ፈንታ መርገም ሠልጥኖ የሰው ዘር በሙሉ በቀቢጸ ተስፋ ተይዞ ተቅበዘበዘ፤ ለመውደቅም ተፍገመገመ። ይሁን እንጂ በአንድ በቀዳማዊ አዳም ምክንያት ሞት እንደ መጣ ሁሉ፤ በአንድ በዳግማዊ አዳም በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምክንያት ሕይወት ሆነ። (፩ ቆሮ. ፲፭፥)

*የተወደችሁ አባቶች ካህናትና ወንድሞች ዲያቆናት፤ የክርስቶስ ቤተ ሰቦች የሆናችሁ ምእመናንና ምእመናት፤*

ለሰው ልጅ ድኅነት ሲል በመስቀል የተሰቀለውን፤ በድል አድራጊነት የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስን ምንጊዜም በልባችን ሰሌዳ በፍጹም ሃይማኖት ከቀረጽነው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ << *ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል።* >> ሲል በማይለወጥ መለኮታዊ ቃሉ ተናግሯልና፤ (ዮሐ.፲፩፥፳፭) ትንሣኤና ሕይወት ለሁላችን ነው። የሕይወት ራስ ወደሆነው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የቀረበ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት አለው። በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አልው ተብሏልና፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የዘለዓለም ሕይወት፤ የሕይወት ራስ፤ ትንሣኤና ሕይወት እንደሆነ በቅድስት ትንሣኤው ተረጋግጧል።

ፀሐይና ጨረቃ፤ መዓልትና ሌሊት በጋና ክረምት የማይፈራረቁባት፤ ዘለዓለማዊ የሆነችውን መንግሥተ ሰማያት ለመውረስ በቅድሚያ በጨለማ ከተመሰለው፤ በሞት ጥላ ሥር ካለው ከኃጢአት ሥራችን ልንላቀቅ ያስፈልጋል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሁልጊዜም መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል በቀራንዮ በመልዕለተ መሰቀል መሰቀሉን፤ ስለእኛም ነፍሱን አሳልፎ መስጠቱን ብቻ ሳይሆን ሞትን አሸንፎ መነሣቱን፤ ድልአድራጊነቱንና ሕያው መሆኑን፤ ዳግመኛም በገርማ መንግሥት ለፍርድ እንደሚመጣ ታስተምረናለች። ስለዚህ መልካም የሆነውን የሃይማኖት ፍሬያችንን ይዘን ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንምጣ። ሰለ እኛ የኃጢአት ካሣ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቅል ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶ፤ ክቡር ደሙን አፍሶ ዋጅቶናልና ሥጋ ወደሙን ከመቀበል አናመንታ። ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለች የኖህ መርከብ፤ የአብርሃም ደንኳን ናትና እንጠጋት፤ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶ ቅዱስ ሥጋና ንጹሕ ደም የተቀደሰች ሰለሆነች እንደ ቅዱስ ያሬድ ሁሉ እኛም ዛሬ *„ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ“* ምድር ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም ታጥባ ፍሲካ ታደርጋለች እያለን እንዘምር። ፋሲካችን ማለት ነጻነታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። በማወቅም ሆነ ወይም ባለማወቅ፤ በበሽታም ሆነ ወይም በድካም፤ በእሥር ቤትም ሆነ ወይም በቁም እሥር ይህን የተቀደሰውን የትንሣኤውን ሌሊት በጸሎትና በዝማሬ፤ በውዳሴና በቅዳሴ በየቤተ ክርስቲያኑ ተገኝተው የማያሳልፉትን ወገኖቻችንን ሁሉ በተቀደሰው ጸሎታችን ልናስባቸው ይገባል።

ውድ ወገኖቼ፤

ሙታን ሕያዋን የሚሆኑበት፤ ሬሳዎች የሚነሡበት ቀን ይመጣልና ደስ ይበለን። „ትንሣኤከ ለዕለ አመነ፤ ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ“ << ትንሣኤህን ለአመን ለእኛ ብርሃንህን ግለጽልን >> እያልን እንዘምር፤

የፍቅር ባለቤት፤ የሰላም ንጉሥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ለውድ አገራችን ለኢትዮጵያ ሰላምን፤ ፍቅርንና አንድነትን፤ ለተሰደዱ መረጋጋትን፤ ላዘኑና ለተከዙ መጽናናትን፤ በሰንሰለት ታሥረው በእሥር ቤት ላሉት መፈታትን፤ ለተራቡት የዕለት ምግብን፥ ለተራቆቱት የዓመት ልብስን፤ ለታመሙት ጤንነትን፤ ለሙታን መልካም ዕረፍትን ያድልልን። በዘር ማጥፋት ወንጀል ከመወነጃጀል ይሰውረን፤ የተቀደሰም ወርኃ ትንሣኤ ይሁንልን። አሜን!

ሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ
በአውሮፓ የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥራ አስኪያጅ